# ከእግዚአብሔር ቃል የጸሎት እቅዶች

*የመዳንንም ራስ ቁር የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው። 18 በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ፤ በዚህም አሳብ ስለ ቅዱሳን ሁሉ እየለመናችሁ በመጽናት ሁሉ ትጉ፤ 19 ደግሞ የወንጌልን ምሥጢር በግልጥ እንዳስታውቅ አፌን በመክፈት ቃል ይሰጠኝ ዘንድ ስለ እኔ ለምኑ፤ ኤፌሶን 6:17-19*

**ቁጥር 1።** *እግዚአብሔርም የይሁዳን አለቃ የሰላትያልን ልጅ የዘሩባቤልን መንፈስ፥ የታላቁንም ካህን የኢዮሴዴቅን ልጅ የኢያሱን መንፈስ፥ የቀሩትንም ሕዝብ ሁሉ መንፈስ አስነሣ፤ . . . የአምላካቸውንም የሠራዊትን ጌታ የእግዚአብሔርን ቤት ሠሩ።* ***ትንቢተ ሐጌ 1:14***

* እግዚአብሔርን በሙሉ ልባችን እንድናፈቅረው ሁሉም አካል በጌታ እንዲነሣ ጸልዩ።. . .

በማንኛውም መንገድ ለብ ያልን እንዳንሆን፥ ነገር ግን ከጌታ ጋር ለመራመድ (አካሄዳችንን ከጌታ ጋር ለማድረግ) በሙሉ ቅንዓት እንድንሞላ ጸልዩ።

**ቁጥር 2።** *ስለዚሁ እኛ ደግሞ ይህን ከሰማንበት ቀን ጀምረን የፈቃዱ እውቀት መንፈሳዊ ጥበብንና አእምሮን ሁሉ እንዲሞላባችሁ እየለመንን፥ ስለ እናንተ ጸሎትን አልተውንም። 10-11 በበጎ ሥራ ሁሉ ፍሬ እያፈራችሁ በእግዚአብሔርም እውቀት እያደጋችሁ፥ 12 ከደስታም ጋር በሁሉ ለመጽናትና ለመታገሥ እንደ ክብሩ ጉልበት መጠን በኃይል ሁሉ እየበረታችሁ፥ በቅዱሳንም ርስት በብርሃን እንድንካፈል ያበቃንን አብን እያመሰገናችሁ፥ በነገር ሁሉ ደስ ልታሰኙ ለጌታ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እንለምናለን።* ***ቆላስያስ 1:9-12***

* ከእግዚአብሔር ጋር ላለን አካሄድ፣ የቤተሰባችን ግንኙነቶች፣ ትምህርት ቤታችን፣ ሥራችን፣ የሥራ ዘርፋችን፣ እና በዚህ አካል(ስብስብ) የእያንዳንዳችን ሥራ ምን እንደሆነ የእርሱን ፈቃድ፤ የት እና እንዴት እግዚአብሔርን እንደምናገለግል የእግዚአብሔር አላማዎችን መገለጥ/ራእይ(በጥበብና በመረዳት) እያንዳንዱ ሰው እንዲያገኝ ጸልዩ።

* ለጌታ የተገባ(የሚገባ) አካሄድ በትሕትና፣ በፍቅር፣ በአንድነት መሄድን(መራመድን) ያጠቃልላል(ይጨምራል) (ኤፌሶን 4:1-3)። ደግሞም መትጋትና "ሁልጊዜ መጸለይን" የአኗኗር ዘይቤ አድርጎ ማጎልመስንም ይጨምራል (ሉቃስ 21:36)።

* ጌታ እያንዳንዳችንን እንድንሠራ በጠራን ሥራዎች ሁላችንም ፍሬያማ እንድንሆን ጸልዩ። በግል ሕይወታችን ብቻ አይደለም ነገር ግን ደግሞ እንደስብስብም፤ ለጌታ በሚሆን አገልግሎት ፍሬያማ እና በምልጃ ጸሎት እንደ "የጸሎት ቤት" ፍሬያማ።

**ቁጥር 3።** *የክብር አባት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እርሱን በማወቅ የጥበብንና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ እለምናለሁ። 18-19 ይህም የልባችሁ ዓይኖች ሲበሩ የመጥራቱ ተስፋ ምን እንዲሆን በቅዱሳንም ዘንድ ያለው የርስት ክብር ባለ ጠግነት ምን እንዲሆን ለምናምን ከሁሉ የሚበልጥ የኃይሉ ታላቅነት ምን እንዲሆን ታውቁ ዘንድ ነው፤* ***ኤፌሶን 1:17-18***

* ይህ ሕልሞችን፣ ራእዮችን እና መገለጦችን ይጨምራል፤ ትንቢታዊ ጥልቅ ማስተዋሎች፣ ብርሃን፣ እና ጌታን ራሱን እና የእርሱን ጥሪ መረዳትን ይጨምራል። በዚህ መንገድ ልባችን በብርሃን ሲጥለቀለቅ፥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ፈልጎ ለመከታተል መንፈሳችን ተነቃቅቶ ደስተኞችና ብርቱዎች እንሆናለን። "ሩጫውን ለመሮጥ" የተበረታታን፣ ሥልጣንና ኃይል የታጠቅን እና ያተኮርን እንሆናለን።

**ቁጥር 4።** *በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታችሁ በኃይል እንድትጠነክሩ ክርስቶስም በልባችሁ በእምነት እንዲኖር እንደ ክብሩ ባለ ጠግነት መጠን ይስጣችሁ፤ የእናንተ ሥርና መሠረት በፍቅር ይጸና ዘንድ፥ 18-19 ከቅዱሳን ሁሉ ጋር ስፋቱና ርዝመቱ ከፍታውም ጥልቅነቱም ምን ያህል መሆኑን ለማስተዋል፥ ከመታወቅም የሚያልፈውን የክርስቶስን ፍቅር ለማወቅ ትበረቱ ዘንድ፥ እስከ እግዚአብሔርም ፍጹም ሙላት ደርሳችሁ ትሞሉ ዘንድ።* ***ኤፌሶን 3:16-19***

*"ጌታችንም ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅዱሳኑ ሁሉ ጋር ሲመጣ፥ በአምላካችንና በአባታችን ፊት በቅድስና ነቀፋ የሌለበት አድርጎ ልባችሁን ያጸና ዘንድ፥ እኛ ደግሞ ለእናንተ እንደምንሆን ጌታ እርስ በእርሳችሁ ያላችሁን ለሁሉም የሚሆን ፍቅራችሁን ያብዛ ይጨምርም።"* ***1ኛ ተሰሎንቄ 3:12-13***

**ቁጥር 5።** *ወንድሞች በኅብረት ቢቀመጡ፥ እነሆ፥ መልካም ነው፥ እነሆም፥ ያማረ ነው።*

*2 ከራስ እስከ ጢም እንደሚፈስስ፥ እስከ አሮን ጢም፥ በልብሱ መደረቢያ እንደሚወርድ ሽቱ ነው።*

*3 በጽዮን ተራሮች እንደሚወርድ እንደ አርሞንዔም ጠል ነው፤ በዚያ እግዚአብሔር በረከቱን ሕይወትንም እስከ ዘላለም አዝዞአልና።* ***መዝሙር 133***

*"ልባቸው እንዲጸናና፥ በፍቅርም ተባብረው በማስተዋል ወደሚገኝበት ወደ መረዳት ባለ ጠግነት ሁሉ እንዲደርሱ የእግዚአብሔርንም ምሥጢር እርሱንም ክርስቶስን እንዲያውቁ እጋደላለሁ። 3 የተሰወረ የጥበብና የእውቀት መዝገብ ሁሉ በእርሱ ነውና።"* ***ቆላስያስ 2:2-3***

* በጋብቻዎች(በትዳሮች)፣ በቤተሰዎች፣ በቤት ቡድኖች፣ በልጆች ቤተክርስቲያን፣ በውዳሴ ቡድን፣ እና በአባላት ውስጥ አንድነት(ኅብረት) እንዲኖር ጸልዩ። ኅብረትን የሚከለክሉ(የሚያስቀሩ) ነገሮችን(ምኞት፣ ሁከት(ጥል)፣ ኩራት(ትዕቢት)፣ ነቀፌታ(ትችት)፣ ፍርሃት፣ መፍረዶች፣ ወዘተ፣) እግዚአብሔር ከልባችን እንዲያወጣ ጸልዩ።

**ቁጥር 6።** *እግዚአብሔር ይላል። በመጨረሻው ቀን እንዲህ ይሆናል፤ ሥጋ በለበሰ ሁሉ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፥ ጎበዞቻችሁም ራእይ ያያሉ፥ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልም ያልማሉ፤*

*18 ደግሞም በዚያች ወራት በወንዶችና በሴቶች ባሪያዎቼ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ ትንቢትም ይናገራሉ።* ***የሐዋርያት ሥራ 2:17-18***

**ቁጥር 7።** እረኛ(መጋቢ) "የክርስቶስ አእምሮ" እንዲኖረው ጸልዩ። የእግዚአብሔር ቃል በአጥንቶቹ ውስጥ እንደ እሳት እንዲቀጣጠል ጸልዩ፤ የጌታን ቃል በመገለጥ ለቅዱሳን ይናገር ዘንድ። በእግዚአብሔር ፍጹም ፈቃድ መሠረት የቤተክርስቲያን ስብሰባችን(ጉባዔያችን) "በቃሉ ውኃ የታጠበ እንዲሆን" ጸልዩ።

http://www.baptizingfire.com , http://fireofgodservants.blogspot.com/ , http://www.thelordshour.com , http://www.choothomas.org , http://www.jesusministries.org/ , http://www.angeltv.org , http://www.Billygraham.org , http://free.messianicbible.com/ , http://www.levitt.tv/ ,

http://www.divinerevelations.info/amharic , http://www.heavenvisit.com , http://www.tribulation-now.org , http://www.voe.org/ , http://www.sidroth.org , http://repentandpreparetheway.org/ , http://www.shekinahworship.com/ , http://www.theblazingholyfire.com/ , http://www.thelastreformation.com ,

http://www.bobjones.org/ , http://www.annarountree.com/ , http://www.beyondthephysicalrealm.com , http://www.shreveministries.org , http://www.blogtalkradio/tribulation-now , http://www.be4thefire.com/ http://www.blogtalkradio/thelordshour , http://www.blogtalkradio.com/discoveringthetruth

**ክብር፥ ኃይል፥ በረከት፥ ምስጋና፥ ጥበብ፥ ማዳን፥ ቅድስና፥ ውዳሴ፥ አምልኮ እጅግ በከበረ ቅዱስ ቡሩክ ዙፋኑ ላይ ላለ የእስራኤል ኃያል አምላክ የሠራዊት ጌታ፥ አንድ አምላክ ለሆነ ለእግዚአብሔር አብ ለእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ለመንፈስ ቅዱስ ይሁን አሜን። ማራናታ ጌታ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ የአብ ቃል የአብ ልጅ ቶሎ ና። ሃሌ ሉያ ክብር ለእግዚአብሔር አብ ሃሌሉያ**

ሊያደርግ የሚገባውን ያደረገ፥ የማይጠቅም ባሪያ ተረኅመው። **ሃሌ ሉያ**